# ለመራጮች ድጋፍ

VOTE 2026

የተለያየ አካል ጉዳተኝነት ላለባቸው መራጮች በግልና ነፃነት ድምጽ የመስጠት በርካታ መንገዶች አሉ።

## የመራጫ ቦታዎች ተደራሽነት

የግዛትና የፌዴራል ህጎች መራጫ ቦታዎች በሰውነት ተደራሽ እንዲሆኑ ይጠይቃሉ። ከተሞችና ከተማዎች በተለምዶ የመራጫ ቦታዎችን ይመርጣሉ እና ለመራጫ ቦታዎች ተደራሽነት ኃላፊ ናቸው።

## ከሌሎች ድጋፍ

ድምጽ ለመስጠት እርስዎን ለመርዳት ማንኛውንም ሰው ሊያመጡ ይችላሉ ወይም ከምርጫ ዳኞች ድጋፍ ማግኘት ይችላሉ። ከአሰሪዎ ወይም ከሠራተኛ ማኅበርዎ ድጋፍ ማግኘት አይችሉም። ረዳትዎ በመራጫ ሂደቱ ሁሉ ሊሳተፍ ይችላል። ረዳቶች እርስዎ ለማን ድምጽ ለመስጠት እንደሚፈልጉ ለማንኛውም ሰው መግለጽ ካልቻሉ እርስዎን እንዴት እንደሚመርጡ ወይም በምርጫ ወረቀቱ ላይ ምልክት ማድረግ አይችሉም።

## በቃል ይግቡ

እርስዎ ማን እንደሆኑ በቃል የማረጋገጥ መብት አለዎት እና ስምዎን መፈረም ካልቻሉ ሌላ ሰው ለእርስዎ እንዲፈርም መጠየቅ ይችላሉ።

## ሞግዚትነት ስር ያሉ መራጮች

ዳኛ በፍርድ ቤት ትእዛዝ የመምረጥ መብትዎን በተለይ ካልወሰደ በስተቀር ሞግዚትነት ስር ሆነው ድምጽ መስጠት ይችላሉ።

### የ2026 ቀናት

የማጣርያ ምርጫ
ማክሰኞ፡ ነሃሴ 11 ቀን

በአካል ሳይገኙ የሚደረግ ምርጫ
በፖስታ መምረጥ ወይም በአካል ተገኝተው የሚመረጥበት ቀን - ከመስከረም 18ቀን እስከ ህዳር 2 ቀን

ለመምረጥ ተመዝገቡ
በዋናው ምርጫ ቀን፡ ግዜ ለመቆጠብ ቀደም ብለው በግዜ እስከ ጥቅምት 13 ቀን ለመምረጥ ይመዝገቡ።

የምርጫ ቀን
ማክሰኞ ህዳር 3 ቀን

ከበስተጀርባ ይቀጥላል...

የሚኖሶታ የአገር ውስጥ አስተዳደር ሚኒስቴር ጽህፈት ቤት

mnvotes.gov • 1-877-600-VOTE

# ለመራጮች ድጋፍ

VOTE 2026

*...ከበፊቱ ገጽ የቀጠለ*

## ተደራሽ የመራጫ ማሽን

የመራጫ ቦታዎች ለእርስዎ ምርጫ ወረቀት ሊያስምሩ የሚችሉ ማሽኖች አሏቸው። በብዕር ድምጽ መስጠት ካልቻሉ (ወይም ካልመረጡ) ግላዊነትን ይሰጥዎታል። ማሽኑ ምርጫ ወረቀቱን በትልቅ ፊደል ወይም በከፍተኛ ንፅፅር ያለው ዳራ ላይ ያሳያል። በአይጢ በኩልም ምርጫ ወረቀቱን ሊያነብልዎ ይችላል። ምርጫዎን በብሬይል ኪይፓድ፣ በተንኳሽ ማያ ገጽ ወይም በመጥባት መሣሪያ መሙላት ይችላሉ። ምርጫዎን ከፈጸሙ በኋላ፣ ማሽኑ የተሟላ ምርጫ ወረቀትዎን ያተምላል።

## በእግር ተዳጅ መንገድ ላይ ድምጽ መስጠት

በቀላሉ ከተሽከርካሪዎ መውጣት ካልቻሉ ምርጫ ወረቀት እንዲያመጡልዎ መጠየቅ ይችላሉ። ይህ 'በእግር ተዳጅ መንገድ ላይ ድምጽ መስጠት' ተብሎ ይታወቃል። ከተለያዩ ትላልቅ ፖለቲካ ፓርቲዎች የተውጣጡ ሁለት የምርጫ ዳኞች ምርጫ ወረቀቱን ያመጡልዎታል። ድምጽ መስጠት ሲጨርሱ፣ የምርጫ ዳኞች የድምጽ መስጫ ወረቀትዎን ወደ ውስጥ ይዘው ወደ ምርጫ ሳጥኑ ያስገባሉ።

## የምትክ ምርጫ ወረቀት ያግኙ

ድምጽዎን ከመስጠትዎ በፊት በምርጫ ወረቀትዎ ላይ ስህተት ካደረጉ የምትክ ምርጫ ወረቀት የማግኘት መብት አለዎት።

## ቅሬታ ያቅርቡ

አንድ ምርጫ በሚካሄድበት መንገድ ካልተደሰቱ በመራጫ ቦታዎ ሪፖርት የማቅረብ መብት አለዎት

ይህን ኮድ ስካን በማድረግ **mnvotes.gov/amharic** ን ይጎብኙ እና ለመምረጥ ይመዝገቡ

*የሚኖሶታ የአገር ውስጥ አስተዳደር ሚኒስቴር ጽህፈት ቤት*

*mnvotes.gov • 1-877-600-VOTE*